ORIGINAL ARTICLE

The Impacts Peer Correction versus Teacher Correction on Students' Writing Performance

Ephriem Tiruneh[1]

Abstract

The general objective of this research was to probe the role of self-peer correction versus teacher correction on students' writing performance. To achieve this objective, grade 9th students of Fasiledes Secondary School were selected by purposive sampling technique. Data was collected using pre and post writing essays test, observation and interview. The data from pre and post writing essay tests were analyzed using descriptive and inferential (independent sample t-test) statistics; the observation and interview data were also analyzed qualitatively. The result of this study revealed that there was significant difference (p=00) between the mean scores of the two groups (self-peer versus teacher) for the post writing essay test. This indicated that teachers' correction had strong effect on students writing performance than self-peer correction. Moreover, the feedback given by peers was found to be unconstructive and less helpful and hence students prefer teacher's correction than self-peer correction. Therefore, the researcher suggests that students' writing can be improved if teachers give accurate and appropriate feedback in a writing lesson.

አህጽሮተ ጥናት: የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት የግለ-ቢጤ እርማትና የመምህር እርማት ስልት የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያላቸውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካትም በጎንደር ከተማ የፋሲለደስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና ተመርጧል፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት በ2010 ዓ.ም. ተመዝግበው የዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች በዓላማ ተኮር ናሙና ተመርጠዋል፡፡ መረጃዎቹ በቅድመና ድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተናዎች፣ በምልከታና በቃለመጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደአግባብነታቸው በመጠናዊና በዓይነታዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡ ዓይነታዊ መረጃዎች በሐተታ ሲገለጹ፣ መጠናዊ መረጃዎቹ ደግሞ በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ (በነፃ ናሙናዎች ቲቴስት) በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ በውጤት ትንተናው መሠረትም በግለ-ቢጤ እርማት ስልት የተለማመዱት ድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤት በመምህር እርማት ስልት ከተለማመዱት የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤት አንፃ ጉልህ ልዩነት (P=0.000) አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የግለ-ቢጤ እርማትን ከተጠቀሙት ተማሪዎች ይልቅ የመምህር እርማት ያገኙ ተማሪዎች ድርሰት መሻሻል እንደታየበት የውጤት ትንተናው አመላክቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት የተማሪዎቹን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ በማጎልበት ረገድ የመምህር እርማት ውጤታማ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ጠቁሟል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎቹ ለቢጤዎቻቸው ድርሰት የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ በሳል እንዳልሆነ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በመጨረሻም ድርሰትን ከግለ-ቢጤ እርማት እና ከመምህር እርማት ስልት አንጻር የተማሪዎች ምርጫ የመምህር እርማት እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ ስለሆነም መምህራን በክፍል ውስጥ በትክክል ተገቢ እርማት መስጠት ከቻሉ የተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ችሎታ እንደሚሻሻል አጥኚው ይጠቁማል፡፡

ቁልፍ ቃላት፤ የመምህር እርማት፣ የግለ-ቢጤ እርማት

መግቢያ

በሰው ልጅ የመማር ታሪክ የግድፈት እርማት በዘመናት ሂደት ሥነባህሪውን እየለወጠ ሄዷል። በ1960ዎቹ መገባደጃ የሰው ልጅ የመማር ማስተማር ሂደት በባህሪያውያን አተያይ (Behaviorist Approach) ተጽዕኖ ስር ወድቆ ነበር። ይህ አተያይ ግድፈት መስራትን ፈፅሞ የማይፈቀድ፣ ሁሌም ትክክለኛ የሆነ ነገር ላይ የሚያተኩር

1 ረዳት ፕሮፌሰር፣ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ሥነጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል መምህር

This journal is licensed under a creative common Attribution-Noncommercial 4.0. It is accredited to the University of Gondar, College of Social Sciences and Humanities.

ፍልስፍና ነበር። ምክንያቱም በተማሪዎች የሚሰሩ ግድፈቶች ወዲያውኑ በመምህሩ ይታረማሉና (Asres 2005)።

ከዚያም ከ1970ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ የባህሪያውያን አተያይ የነበረው ዝና እየከሰመ ሄዶ አዕምሯዊ አተያይ (Cognitive approach) በምትኩ ስፍራውን ያዘ። ይህም አተያይ ግድፈትን እንደተለመደ የሰው ልጅ ባህሪ የሚቆጥርና ለእርማት ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን፣ ለመማር ማስተማር ሂደቱ ጠቀሜታው እየጎላ በመምጣቱ የተለያዩ የቅርብ ጊዜ ጥናቶች በግድፈት እርማት ረገድ የአዕምሯዊ አቀራረብን እሳቤ እንደሚደግፉ Asres (2005) McArthur (1983)ን ጠቅሰው ያስረዳሉ።

ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች የሚፈጠሩ ግድፈቶች የትምህርት አካል እንደሆኑና የሚከሰቱትም ግድፈቶች መታረም እንዳለባቸው የሚያመላክቱ ተመራማሪዎች አሉ። Edge (1989) ግድፈት መስራት የቋንቋ መማር አንዱ አካል እንደሆነና ብዙ ሰዎችም እንደሚስማሙበት ያስረዳሉ። በእርግጥ እርማት ለመማር ማስተማር ሂደቱ የሚኖረው ድርሻ አጠያያቂ አይደለም። አንድ ተማሪ ከሚፈፅመው ግድፈት መማር የሚችለው ደግሞ መምህሩ ወይም ቢጤው ግድፈቱን በመለየት በሚሰጠው ገንቢ አስተያየት እንደሚሆን ይታመናል።

ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በሚለማመዱበት ወቅት ግደፈቶች ሳይከሰቱ እንደማይቀሩ Harmer (1991)፣ Raimes (1985) እና Edge (1989)፣ ከሚያስገነዝቡ ባለሙያዎች ጥቂቶቹ ናቸው። ለግድፈቶች እርማት መስጠት ደግሞ አስፈላጊ መሆኑን በርካታ ጸሐፍት (Edge 1989፣ Byrne 1988፣ Makino 1993፣ Ur 1999) ይስማማሉ። በተለይ Edge (1989)፣ Ur (1999)፣ Atkins et al. (1996) በመጻፍ ወቅት የበርካታ ዓረፍተ ነገሮችን ትርጉም የሚያፋልሱ ስህተቶችን (mistakes) ማረም ተገቢ ነው በማለት ያስረዳሉ።

መምህራን በተለምዷዊው (traditional) የእርማት ስልት የተማሪዎችን ድርሰት ሙሉ በሙሉ ለማዳረስ ጥረት ስለሚያደርጉ፣ ለመምህራን ጊዜ ጨራሽ ሲሆን፣ ለተማሪዎች ደግሞ ተስፋ አስቆራጭ ነው (Byrne 1988፣ Ur1999)። ከዚህ በተጨማሪ Cohen and Cavalcanti (1987) ተደጋጋሚ የሆነ የመምህራኑ ግብረ መልስ የተማሪውን የመጻፍ መሻሻል እንደማያረጋግጥ Graham(1983)ን ዋቢ በማድረግ ያስረዳሉ። በተቃራኒው Maarof et al. (2011) መምህሩ የሚሰጠው እርማት የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ በማጎልበት በኩል መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነና ከግልና ቢጤ የእርማት ስልቶች ይልቅ የመምህሩ እርማት የተሻለ፣ እንዲሁም ተማሪዎቹ ለመምህር እርማት ከፍተኛ ቦታ እንደሚሰጡ ይገልፃሉ፡፡

Edge (1989) በመምህር ከሚደረገው የእርማት ስልት በተጨማሪ የግልና የቢጤ የሚባሉ የእርማት ዓይነቶች እንዳሉ ያስረዳሉ። በተለይ እነዚህ ሁለት የእርማት ዓይነቶች የመጻፍ ክሂልን ከማሻሻል ባሻገር የመምህራንን የስራ ጫና እንደሚያቃልሉ በርካታ ጸሐፍት (ለምሳሌ፤ Raimes 1983፤ Edge 1989፤ Byrne 1988፤ Norrish 1983) ያስገነዝባሉ። በተጨማሪም ሰለሞን (1987፣16) Lalande(1982)ን ዋቢ በማድረግ "ለተማሪዎች [ስህተቶችን] የእርማት መረጃ ምገባ ማካሄድ የመምህሩ ተግባር ብቻ ባለመሆኑ ተማሪዎች ራሳቸው [ስህተቶቻቸውን] እንዲያርሙና ትክክለኛውን አጠቃቀም በግላቸው እንዲፈልጉ ማድረግ ለሁለቱም ወገኖች ጠቃሚ ይሆናል።" በማለት ያስረዳሉ።

Alwright (1987)ን ጠቅሰው Makino (1993) እንዳሰፈሩት የተማሪዎች ግድፈት መታረም ይኖርበታል፤ ሆኖም ተማሪዎች የራሳቸውን ግደፈት የሚያርሙ ከሆነ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ግራ መጋባት ማስወገድ እንዲችሉ ግልጽ የሆኑ የማስተማሪያ ክፍል ስልቶችና (classroom strategies) ቋሚ የእርማት መመሪያዎች ያስፈልጓቸዋል።

ተማሪዎች የራሳቸውን ግድፈቶች እንዲያርሙ መምህራን ዕድሉን ሊሰጧቸው እንደሚገባም በርካታ ተመራማሪዎች (ለምሳሌ፤ Edge 1989፣ Makino 1993፣ Raimes 1983፣ Norrish 1983፣ Maxwell 1996) ያስገነዝባሉ።

Witbeck (1976) አራት ዓይነት የቢጤ እርማት ስልቶችን በፍትነታዊ ጥናት ፈትሸዋል። ባካሄዱት ጥናት በዚህም ተማሪዎችን በቢጤ እርማት እንዲሳተፉ በማድረግ ከፍተኛ ደረጃ ያለው የመጻፍ ፍሰትና (writing fluency) ጥሩ የክፍል ውስጥ ድባብ መፍጠር እንደተቻለ አረጋግጠዋል።

Witbeck (1976) በዚሁ ጥናታቸው Maize (1992)ንጠቅሰው እንዳሰፈሩት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ ትኩረት ባደረገ ክፍል ውስጥ የሚካሄድን የቢጤ እርማት ከክፍል ውጭ ከሚደረግ የመምህር እርማት ጋር ንጽጽራዊ ጥናት አካሄደዋል። በተገኘውም ውጤት መሠረት የተማሪዎች እርማት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ በተጨማሪ

Graner(1978) የዶክተሬት ድግሪ ማሚያና ሌሎች የተለያዩ ጥናቶችን ከልሰው እንዳቀረቡት ድርሰቶቻቸው በቢጤዎቻቸው የታረሙላቸው ተማሪዎች በመምህር ከታረመላቸው ተማሪዎች የበለጠ ከፍተኛ የመጻፍ ችሎታ አሳይተዋል (ለምሳሌ፤ Ford 1973፣ Lagana 1974፣Pflaum 1980፣Elias 1981፣Weeks & White 1982፣Chaudron 1993)።

በተቃራኒው Roessler (1983)፣ Pianko & Radzik (1980) እንደሚያስረዱት ተማሪዎቹ የችሎታ እጥረት ስላላቸው ውጤታማ እርማት ለመስጠት አይችሉም፤ በመሆኑም በተማሪዎች የሚደረግ እርማት ከጥቅም ጉዳቱ ያመዝናል። Nelson & Murphy (1993) በበኩላቸው የቢጤ እርማትን ውጤታማነት መናገር የተወሳሰበ ጉዳይ እንደሆነ ይገልፃሉ። በተጨማሪ በFerris (2003) የተጠቀሱት Conur and Senavegin (1994) በመምህር እርማት ስልትና በግለ-ቢጤ እርማት መካከል ልዩነት መኖሩን፣ እንዲሁም ተማሪዎቹ ከእርማት በኋላ በድርሰታቸው ላይ ምን ዓይነት ለውጥ ያስከትላሉ? የሚለውን ለመፈተሽ ባካሄዱት ንጽጽራዊ ጥናት የግለ-ቢጤ እርማት በተማሪዎች ድርሰት ላይ የሚያስከትለው ለውጥ እጅግ አነስተኛ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

እንደ Brooks & Grundy (1990) አገላለፅ ደግሞ በመጻፍም ሆነ በንግግር ጊዜ ግለ እርማት ከቢጤ እርማት፣ እንዲሁም የቢጤ እርማት ከመምህር እርማት ተመራጭ (preferable) ይሆናል። በመጻፍ ክሂል ወቅት ደግሞ በጣም አስፈላጊው ግለ እርማት ነው። ስለሆነም መምህራን በክፍል ውስጥ ለግለ እርማት ከፍተኛ ዕድል መስጠት ይኖርባቸዋል።

Lewis and Hill (1985) በመርሀ ደረጃ ግለ እርማት ከሌሎች የተሻለ መሆኑን በማስረዳት የBrooks & Grundy (1990)ን ሐሳብ ያጠራክራሉ። በሌላ በኩል Italo (1999) የቢጤና የመምህር እርማት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እንደሚያጎለብት በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ በአንፃሩ ግለ እርማትና የቢጤ እርማት ካልተሳኩ መምህራን ራሳቸው ግድፈቶችን ማረም ይችላሉ (Atkines et al. 1996፣Edge 1989)።

Makino (1993) 62 በሚደርሱ የአንደኛ ዓመት ጃፓናዊያን የኮሌጅ ተማሪዎች የራሳቸውን ግድፈት እንዲያርሙ በተደረገ ጥናት ተማሪዎች በግለ እርማት በከፍተኛ መጠን ውጤታማ እንደሆኑ ቢያረጋግጡም፣ እኒሁ አጥኚ Log (1997)ን ዋቢ በማድረግ ግድፈትን ማከም (treatment) በጣምም አስፈላጊ እንዳልሆነና ሌሎች ጸሐፍትም (Krashen 1982፣ Krashen & Terrel 1983) በግድፈት እርማት ላይ ተመሳሳይ ጥርጣሬ እንዳላቸው ያስረዳሉ። በሌላ በኩል Chun(2004)ን፣ Rivers& Timperley (1978)ን ጠቅሰው Asres (2005) እንዳቀረቡት በግል፣ በቢጤና በመምህር እርማት ውጤታማነት ላይ በተካሄደ ፍትነታዊ ጥናት ከሦስቱ የተሻለ እርማት የሚባል እንደሌለ አረጋግጠዋል።
በኢትዮጵያም የግልና ቢጤ እርማትን ለየብቻ፣ እንዲሁም የግልና የቢጤ እርማትን በማቀናጀት ለማጥናት የሞከሩ አሉ። ሰለሞን (1987) የቢጤ እርማትን ተግባራዊነትና ውጤታማነትን በ11ኛክፍል ተማሪዎች ላይ ፍትነታዊ ጥናት አካሂደዋል። በውጤቱም ተማሪዎቹ የቢጤ እርማትን አሰራር የሚደግፉና የሚቀበሉት መሆናቸው እንጂ በክሂል ረገድ መሻሻል እንዳልተመዘገበ አረጋግጠዋል። ተሻገር (2001) በበኩላቸው የግለ እርማት ስልት የተማሪዎችን [የጽህፈት] ክሂል በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን በጥናታቸው ጠቁመዋል። እንዲሁም ኤፍሬም (2000) የግልና የቢጤ እርማት የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ እንዳሻሻለ በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡

በተጨማሪም Mesfin (2004) የግል እርማትንና የቢጤ እርማትን ውጤታማነት በ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ለመፈተሽ ንጽጽራዊ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ሁለቱ የእርማት ስልቶች የተማሪዎችን ድርሰት በማሻሻል ረገድ ጠቃሚ መሆናቸውን ከጻፉት ድርሰት የተገኘው መረጃ አመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከመምህራን መጠይቅ የተገኘው መረጃ ደግሞ ግድፈቶችን በማረም በኩል ከግል እርማት ይልቅ የቢጤ እርማት የተሻለ መሆኑን ሲያመላክት፣ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘው መረጃ ደግሞ ተማሪዎች ከሁሉም የእርማት ስልቶች መካከል በቅድሚያ የመምህር እርማትን እንደሚመርጡ ሲያሳይ፣ ከግልና ከቢጤ እርማት ደግሞ የቢጤ እርማትን እንደሚመርጡ ጥናቱ አመልክቷል፡፡ Hyland & Hyland (2006) በተማሪዎች ምርጫ ላይ የተካሄዱ ጥናቶችን ከልሰው እንዳቀረቡት፣ ተማሪዎች የመምህራንን እርማት እንደሚሹና ይህ ካልሆነ ግን የመጨናነቅ ስሜት የሚታይባቸው መሆኑን ይገልጻሉ (ለምሳሌ፤ Ferris 1995; Hyland 1998; Lee 2004; Ferris and Roberts 2001)፡፡

በሌላ በኩል Tesfaye (1999) በበኩላቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንግሊዝኛን የሚያጠኑ 32 የመጀመሪያ ድግሪ ተማሪዎችን በመውሰድ የግልና የመምህር እርማት ስልት በተማሪዎች ጽሑፍ ላይ ያለውን ውጤታማነት

ለመፈተሽ የ10 ሳምንታት ፍትነታዊ ጥናት አካሄደዋል፡፡ በውጤቱም የግል እርማት ስልት የተጠቀሙ ተማሪዎች በመጻፍ ክሂላቸው ላይ መሻሻል አሳይተዋል፡፡

ደምሴ (1962)ን፣ Karegianes et al. (1980)ን ዋቢበማድረግ ሰለሞን (1987) እንደሚያብራሩት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በድርሰት ጽህፈት ረገድ አያሌ ችግሮች የሚገጥማቸው ከዝቅተኛ ክፍሎች ጀምሮ በየደረጃው በቂ የመፃፍ፣ የማንበብና ያነበቡትንም የመመርመርና የመተቸት ልምድ ባለማግኘታቸው ነው። ማረው (1996) በበኩላቸው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመፃፍ ክሂል ትኩረት እንዳነሰውና በዚህ ረገድም የተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ደካማ እንደሆነ በመስኩ ምርምር ያካሄዱ ተመራማሪዎችን (አምሳሉና ደምሴ 1982፣ ዓለማየሁ 1986፣ ክፍሌ 1988) በመጥቀስ ያብራራሉ።

ቀደም ሲል እንደተጠቆመው የግል፣ የቢጤ እና የመምህር እርማት የመጻፍ ክሂልን እንደሚያጎለብቱ ቢታወቅም፣ በኢትዮጵያ የግለ-ቢጤ እርማት እና የመምህሩ እርማት ውጤታማነትን በንጽጽር ጥናት ምን እንደሚመስል ለማየት ሲሞከር አጥኚው አላስተዋለም። እንዲሁም በጥምረት ባይሆንም ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር እግረ መንገዳቸውን ተያያዥነት ያላቸው የምርምር ስራዎች ቢኖሩም እጅግ በጣት የሚቆጠሩ እንደሆኑ አጥኚው ካደረገው ዳሰሳ ለመታዘብ ችሏል፡፡ ከዚህም ሌላ በውጭ ሃገራት በተጠኑት ጥናቶች የተገኘው ውጤት ወጥ አለመሆኑና በእኛ ሀገር በተለይ ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ አውድ ጥናቱ ቢካሄድ ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለው አጥኚው ይህን ጥናት እንዲያካሂድ ምክንያት ሆኖታል፡፡ በተጨማሪም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂልን በሚያስተምሩበት ጊዜ ተማሪዎች የራሳቸውንና የቢጤዎቻቸውን ድርሰት እንዲያርሙ እንደማያደርጉ ከሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር ባደረገው ኢ-መደበኛ ውይይት መረዳት በመቻሉ ይህን ጥናት በዚህ ወቅት ማካሄድ ተገቢ እንደሆነ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል።

ይህ ጥናት ከቦታና ከትምህርት ቤት አኳያ ያተኮረው በጎንደር ከተማ በሚገኘው በአመቺ ናሙና በተመረጠው በፋሲለደስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ነው፡፡ የክፍል ደረጃው በዓላማ ተኮር ናሙና፣ እንዲሁም በቀላል የዕጣ ናሙና በተመረጡ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በግለ-ቢጤ እርማት ለሚለማመዱት ተማሪዎች ከእርማቱ ጋር የተያያዘ የድርሰት ትምህርት ተሰጥቷል። ስለድርሰት እርማት መመሪያም በአጥኚው ማብራሪያ እንዲያገኙ ተደርጓል። ስለዚህ ይህ ጥናት መጻፍን በመማር ማስተማር ሂደት የግለ-ቢጤ እርማት እና የመምህር እርማት ያላቸውን ውጤታማነት በመፈተሽ ላይ ብቻ ያነጣጠረ በመሆኑ ከዝርዝር የድርሰት አጻጻፍ ዘዴዎችና ውጤታማነታቸው በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን አልተመለከትም።

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት የግለ-ቢጤ እርማትና የመምህር እርማት ስልት ያላቸውን ውጤታማነት በንጽጽር በማጥናት ከሁለቱ የትኛው የተሻለ ሊሆን እንደሚችል ማሳየት ነበር፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል፡-

- የግለ-ቢጤ እርማትንና የመምህር እርማት ስልትን ተጠቅመው ድርሰት ከሚጽፉ ተማሪዎች የየትኞቹ ድርሰት ይበልጥ ይሻሻላል?
- ድርሰትን በግለ-ቢጤ እርማት ወይም በመምህር እርማት ከማሳረም አንፃር የተማሪዎች ምርጫ ምንድን ነው?
- በግለ-ቢጤ እርማት ላይ ተማሪዎቹ የሚሰጧቸው አስተያየቶች ምን ይመስላሉ? የሚሉት ነበሩ፡፡

የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት በዓይነቱ አወዳዳሪ ምርምር (comparative study) ነው፡፡ ጥናቱ ፍትነት መሰል (Quasi-experimental) ስልት ላይ የተመሠረተ ሁለት የሙከራ ቡድኖች (ሙከራ ቡድን አንድና ሙከራ ቡድን ሁለት) ቅድመ ልምምድና ድህረ ልምምድ ፈተና የምርምር ንድፍን (two groups pretest-posttest design) የተከተለ ነው፡፡ በሁለቱ ቡድኖች ቅድመ ልምምድና ድህረ ልምምድ ፈተና የምርምር ንድፍ መሠረትም ሁለቱ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አንድ ዓይነት ቅድመ ልምምድ የድርሰት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ከዚያም የሙከራ ቡድን አንድ ተማሪዎች በግለ-ቢጤ እርማት፣ የሙከራ ቡድን ሁለት ተማሪዎች ደግሞ በመምህር እርማት ስልት ተለማምደዋል፡፡ በመጨረሻም የሁለቱ ቡድኖች ተማሪዎች አንድ ዓይነት ድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተና ተፈትነዋል፤

የጥናቱ ተሳታፊዎች

በጎንደር ከተማ ከሚገኙት የሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል የፋሲለደስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና ተመርጧል፡፡ አመቺ ናሙና ተግባራዊ የተደረገበት ምክንያት ጥናቱ ፍትነታዊ ከመሆኑ አንጻር ረጅም ጊዜ ስለሚጠይቅ ትምህርት ቤቱ ፈቃደኛ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት በ2010ዓ.ም. በመማር ላይ ከሚገኙት 22 የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች መካከል የሁለት የመማሪያ ክፍሎች (9ኛ4 እና 9ኛ13) በቀላል ዕጣ የናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ በሁለቱ ምድቦች 143 ተማሪዎ ይገኛሉ፡፡ ከዚያም በቅድመ ልምምዱ የድርሰት ፈተና ያላቸው አማካይ ውጤት በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ቀመር ተሰልቶ መሠረታዊ ልዩነት የሌለው ሆኖ ስለተገኘ በቀላል ዕጣ የንሞና ዘዴ የአንዱ መማሪያ ክፍል 75 ተማሪዎች የሙከራ ቡድን አንድ (9ኛ4) ሌላው ደግሞ 68 ተማሪዎች የሙከራ ቡድን ሁለት (9ኛ13) ተብለው ተከፍለዋል፡፡

ተጠኚዎቹ ከላይ በተገለፀው መንገድ ተለይተው ከታወቁ በኋላ አንደኛው ቡድን በግለ-ቢጤ የእርማት ስልት እንዲለማመድ ሲደረግ፣ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ በመምህር የእርማት ስልት እንዲለማመድ ተደርጓል፡፡ በግለ-ቢጤ የተለማመደው የሙከራ ቡድን አንድ በመጀመሪያ በጻፉት ድርሰት ላይ በግለ እርማቱ ቅጽ መሠረት የራሳቸውን ድርሰት አርመዋል፤ በእርማቱ መሠረት ድርሰታቸውን እንደገና አሻሽለው በጻፉት ድርሰት ላይ ቢጤዎቻቸው እርማት እንዲያከናውኑ ተደርጓል፡፡ ከቢጤ እርማቱ ሂደት በኋላ ረቂቁ ድርሰት ከማረሚያ ቅጹ ጋር ለድርሰት ጸሐፊው እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም የድርሰቱ ባለቤት የቢጤውን የእርማት አስተያየት ባገናዘበ መልኩ በድጋሜ በድርሰቱ ላይ ግለ እርማት በማካሄድ የመጨረሻውን ድርሰት አሻሽሎ እንዲጽፍ ሆኗል፡፡ በዚሁ አኳሃን ተማሪዎቹ በተመረጠላቸው የእርማት ስልት መሠረት ለስድስት ሳምንት፣ በሳምንት ሁለት ቀን (በቀን ሁለት ሠዓት) እንዲለማመዱ ተደርጓል፡፡ በዚህም በአራት የተለያዩ የመጻፊያ ርዕሶች (የአለባበስ ባህላችን፣ የልጅነት ትዝታ፣ ጓደኛዬ እና ቤታችን) ድርሰት ጽፈዋል (የመጀመሪያና የመጨረሻ ረቂቅ)፡፡ የሙከራ ቡድን አንድም ሆነ የሙከራ ቡድን ሁለት ተማሪዎች ቀድመው ሲያስተምሯቸው በነበሩ መምህራን ልምምዱን አከናውነዋል፡፡ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑን ያስተማሩት ሁለት መምህራን አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ዲግሪ ያላቸው ናቸው፡፡ የሙከራ ቡድን ሁለት መምህርት አማርኛ በማስተማር የ12 ዓመት ልምድ የነበራቸው ሲሆን፣ የሙከራ ቡድን አንድ መምህርት ግን የነበራቸው የማስተማር ልምድ 9 ዓመት ብቻ ነበር፡፡ በግለ-ቢጤ የእርማት ስልት የሚለማመዱት ተጠኚዎች የሚሰጡት የእርማት አስተያየት መሪ ጥያቄዎችን መሠረት በማድረግ ስለሆነ የእርማት መመሪያ ተዘጋጅቶ ተሰጧቸዋል፡፡ ተጠኚዎች ወደመደበኛ ልምምዱ ከመግባታቸው በፊት ስለድርሰት እርማት መመሪያ ለሁለት ቀን (በቀን ሶስት ሠዓት) በአጥኚው ማብራሪያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ልምምዱ የጀመረው በግለ እርማት ሲሆን፣ ተማሪዎቹ በግል የድርሰት ረቂቅ እንዲፅፉ ተደርጓል። ተማሪዎቹ በፃፉት ረቂቅ ላይ ግለ እርማት በማካሄድ ድርሰታቸውን አስተካክለዋል፤ ተጠኚዎቹ ይህን ግለ እርማት ያካሄዱበትን የድርሰቱን ረቂቅ በመለዋወጥ ለቢጤ ቡድኖቹ አቅርበዋል፡፡ የቢጤ እርማት የተደረገበት የድርሰቱ ረቂቅ ለድርሰት ባለቤቱ በድጋሜ በመስጠት ግለ እርማት እንዲያካሄድበት ተደርጓል፡፡ በዚህም እርማቱ ዑደታዊ አሰራርን የተከተለ ነበር፡፡ በቢጤ እርማቱ ወቅት በአንድ ቡድን አራት ተማሪዎች የተደራጁ ሲሆን፣ በቡድኖች ያለው የአሰራር ቅደም ተከተል Hedge(1988፤158) በሚያቀርቡት መንገድ ሆኗል፡፡ የድርሰት እርማት መመሪያው ደግሞ በዋናነት ከድረ ገጽ (ims.ode.state.oh.us/oDE.IMS/Lessons/content/CEW-LP-So1-BD-L-10-I15-01.pdf-) የተገኘውን ድርሳን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው (አባሪ "ሀ" ይመለከቷል)፡፡

ሁለተኛው ቡድን በመምህር የእርማት ስልት የተለማመደ ሲሆን፣ ተማሪዎቹ በጻፉት ድርሰት ላይ መምህሩ እርማት ሰጥቷል፡፡ እርማቱ ግድፈት ያለበትን ቦታ ከስሩ አስምሮ በማመልከት ወይም በወረቀቱ ህዳግ ላይ ፍንጮችን በማመልከት ወይም ሁለቱንም በመጠቀም የተከናወነ ነው፡፡ ተማሪዎቹም በእርማቱ አስተያየት መሠረት ድርሰታቸውን አሻሽለው ጽፈዋል፡፡ መምህሩም ተማሪዎቹ የፃፏቸውን ድርሰቶች (የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን ረቂቅ) ለአጥኚው አስረክቧል፡፡

የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

የጥናቱን ዓላማ መሠረት በማድረግ መረጃ እንዲያስገኙ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪዎች የቅድመና ድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተናዎች፣ ሰነድ ፍተሻና ቃለመጠይቅ ናቸው።

የጥናቱ ዋና ዓላማ የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ረገድ የግል-ቢጤ እርማትና የመምህር እርማት ስልት የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያላቸውን አስተዋጽኦ በንጽጽር በመፈተሽ ከሁለቱ የትኛው የተሻለ ሊሆን እንደሚችል ማሳየት ነው። በዚህ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመገንዘብ ቅድመ ፈተና እንዲፈተኑ ሆኗል። Madsen (1983) እና Heaton(1990) እንደሚያስገነዝቡት የመጻፍ ክሂልን ለመመዘን

ከሚወሰዱት መፍትሄዎች አንዱ የድርሰት ፈተና ነው። በዚህም መሠረት ተማሪዎቹ "የትውልድ ሰፈሬ" በሚል ተመሳሳይ ርዕስ ድርሰት እንዲጽፉ ተደርጓል። የመጻፊያ ርዕሱም የተማሪዎችን አጠቃላይ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጀ ነው። እንዲሁም ልምምዱን ካጠናቀቁ በኋላ በመጻፍ ክሂል ረገድ ያሳዩትን መሻሻል ለመፈተሽ በጥናቱ ማብቂያ ላይ "የፈተና ሰሞን" በሚል ርዕስ ድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል። የተማሪዎቹ የጽሑፍ ፈተናም ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰበው ፈተናም ከአንድ ድርሰት ገምጋሚ መምህር ጋር በመሆን እርማቱ ተከናውኗል፡፡ ድርሰት ገምጋሚ መምህር ማሳተፍ የተፈለገው ውጤቱን ከአድሎ የጸዳ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡ በመቀጠልም አጥኚው ከዚህ የተማሪዎችን ጽሑፍ ከሚገመግመው መምህር ጋር በመሆን በተንታኝ ዘዴ (analytic approach) እርማቱን አከናውኗል፡፡ ለአስተራረሙ ወጥነት ያግዝ ዘንድ የማረሚያ ቅጽ ተባዝቶ ለአራሚዎቹ ተሰጥቷል፡፡ የመገምገሚያ ቅጹ በዋናነት Jacobs et al. (1981) ባሰናዱት የመገምገሚያ ቅጽ ላይ ተመስርቶ ለዚህ ጥናት እንዲስማማ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም የመገምገሚያ ቅጹ ይዘት (content)25%፣ አደረጃጀት (organization)20%፣ የአጻጻፍ ስልት (style)20%፣ ሰዋስው (grammar)15%፣ የፊደላት ግድፈትና አጻጻፍ (15%)፣ የጽሑፍ ቅርጽ (5%) የሚሉ የትኩረት ነጥቦችና የውጤት መመዝገቢያ አሃዞች አሉት፡፡ ይህንን የድርሰት መገምገሚያ ቅጽ Wening (2016)ም ተጠቅመውበታል፡፡ የአስተራረም መንገዱም የአንድን ተማሪ የመልስ ወረቀት በሁለት ቅጂ ተራብቶ ለሁለቱ አራሚዎች እንዲደርስ በማድረግ ነው፡፡ የቅድመና ድህረ ፈተናው የታረመው ከ100 ነበር፡፡ በሁለቱ አራሚዎች መካከል ያለው ስምምነት በአራሚ ዘለል በpearson r ቀመር 0.805 አስተማማኝነት ተመዝግቦበታል፡፡ በዚህም መሠረት በአራሚዎች መካከል ያለው የአራሚ ዘለል ስምምነት ከተሰላና ተቀባይነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ሁለቱ አራሚዎች ለአንድ ተማሪ የሰጡት ውጤት ለሁለት ተካፍሎ የተገኘው አማካይ ነጥብ የተማሪው ውጤት ተደርጎ ተመዝግቧል፡፡

ሰነድ ፍተሻ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ነው፡፡ ይህም የተመረጠበት ምክንያት በልምምዱ ወቅት ከእርማቱ ጋር በተያያዘ ተማሪዎቹ የሚሰጡት አስተያየቶች ምን እንደሚመስሉ ለማየት ነው፡፡

በዚህ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ በተግባር ላይ ከዋሉት መሣሪያዎች አንዱ ቃለመጠይቅ ነው። የቃለመጠይቁ ዓላማም የሙከራው ቡድን አንድ ተማሪዎች በግለ-ቢጤ የእርማት ስልት ከተለማመዱ በኋላ የእርማት ስልቱ ምን ያህል ድርሰት የመጻፍ ችሎታቸውን ለማሻሻል እንደጠቀማቸው አስተያየታቸውን እንዲሰጡና የእርማት ስልት ምርጫቸውን እንዲገልጹ ለማድረግ ነው፡፡ ተጠኚዎቹ ስሜታቸውን ይበልጥ ነጻ በሆነ መልኩ ይገልጻሉ በሚል እሳቤ የተዘጋጀው ቃለመጠይቅ በዋናነት በከፊል የተዋቀረ የሚባለው ዓይነት ነው፡፡ በቀላል የዕጣ ንሞና ስልት መሠረት አምስት ቃለመጠይቅ የሚደረግላቸው ተማሪዎች ከተመረጡ በኋላ በአጥኚው አማካይነት ቃለመጠይቁ ተካሂዷል፡፡ ተማሪዎቹ የሰጧቸው ምላሾች በመቅረጸ ድምጽ ተቀድተዋል፣ በማስታወሻ ደብተር ላይም ተገልብጠዋል፡፡

የመረጃ አተናተን ዘዴ

የቅድመና ድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይት በነፃ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልተዋል። እንዲሁም በቃለመጠይቁና በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡት መረጃዎች በሐተታ ተገልጸዋል።

የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ክፍል ለጥናቱ የተሰበሰቡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ በቅደም ተከተል ይቀርባሉ፡፡

	ቡድን	የናሙና ብዛት	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የቲ-ዋጋ	የነጻነት ደረጃ	የጉልህነት ደረጃ
ቅድመ ልምምድ የድርሰት ፈተና	አንድ	75	23.73	8.95	1.567	141	0.572
	ሁለት	68	22.89	8.64			

የውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት አንደኛው መሠረታዊ ጥያቄ “የግለ-ቢጤ እርማትንና የመምህር እርማት ስልትን ተጠቅመው ድርሰት ከሚጽፉ ተማሪዎች የየትኞቹ ድርሰት ይበልጥ ይሻሻላል?” የሚል ነበር፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ የመጀመሪያው የትንተናው ክፍል ያተኮረው ለጥናቱ የተመረጡት የሁለት ቡድኖች ተማሪዎች በተለያዩ ስልቶች እርማት ከማግኘታቸው በፊት በመጻፍ ችሎታ መሠረታዊ ልዩነት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን በመፈተሽ ላይ ነው፡፡ በዚህም መነሻነት መረጃው በገላጭና ድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኖ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 1፤ የሙከራ ቡድን አንድና የሙከራ ቡድን ሁለት የቅድመ ልምምድ የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነፃ ናሙናዎች ቲ-ቴስት

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው የሙከራው ቡድን አንድ ተማሪዎች የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤት (23.73) ከሙከራው ቡድን ሁለት ተማሪዎች አማካይ ውጤት (22.89) በ0.84 በልጦ ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም የሙከራው ቡድን አንድ ተማሪዎች የድርሰት ፈተና መደበኛ ልይይት (8.95) ከሙከራ ቡድን ሁለት ተማሪዎች መደበኛ ልይይት (8.64) በ0.31 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም ውጤት በተራ ምልከታም ቢሆን በሁለቱ መካከል ሰፊ ልዩነት ያላቸው ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ በሙከራ ቡድን አንድና በሙከራው ቡድን ሁለት ተማሪዎች የቅድመ ልምምድ የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን የነፃ ናሙናው ቲ-ቴስት ውጤቱ (t(141)=1.567, P=0.572) አሳይቷል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድን አንድና የሙከራው ቡድን ሁለት ተማሪዎች ድርሰት በመጻፍ ችሎታቸው ልዩነት እንደሌላቸው ነው፡፡

በዚህ መልኩ ቡድኖቹ በቅድመ ልምምድ ድርሰት የመጻፍ ችሎታቸው የጎላ ልዩነት አለመኖሩ ከታወቀ በኋላ ሁለቱ ቡድኖች በተለያየ የእርማት ስልት ለስድስት ሳምንታት ሲለማመዱ ቆይተው ድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ በዚህም መሠረት የድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተናው መረጃ በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኖ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 2፤ የሙከራ ቡድን አንድና የሙከራ ቡድን ሁለት የድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤቶች ልዩነቶች በነፃ ናሙናዎች ቲ-ቴስት

	ቡድን	የናሙና ብዛት	አማካይ ውጤት	መደበኛ ልይይት	የቲ-ዋጋ	የነጻነት ደረጃ	የጉልህነት ደረጃ
ድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተና	አንድ	75	37.72	9.346	9.047	141	0.000
	ሁለት	68	53.87	11.946			

ሰንጠረዥ ሁለት እንደሚያሳየው የሙከራው ቡድን ሁለት የድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤት (53.87) ከሙከራ ቡድን አንድ አማካይ ውጤት (37.72) ከፍ ያለ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በዚሁ ሁለቱ ቡድኖች በቅድመ ልምምዱ የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤትና በድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል የውጤት ጭማሪ እንዳለ ማጤን ይቻላል፡፡ ሆኖም በቡድኖቹ የቅድመና ድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ መረጃው በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተፈትሿል፡፡ ይኸውም በሙከራው ቡድን ሁለት ተማሪዎች የቅድመ ልምምድ የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t(141)=9.047, P=0.000) አሳይቷል፡፡ ይህም ከሙከራ ቡድን አንድ ተማሪዎች ይልቅ የሙከራው ቡድን ሁለት ተማሪዎች ድርሰት በመጻፍ በኩል መሻሻል ያሳዩ መሆኑን ነው፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄ “ድርሰትን በግለ-ቢጤ እርማት ወይም በመምህር እርማት ከማሳረም አንፃር የተማሪዎች ምርጫ ምንድን ነው?” የሚል ነበር፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ በቃለመጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በዓይነታዊ መረጃ ተተንትኗል፡፡ በቃለመጠይቁ በተገኘው መረጃ መሠረትም ተማሪዎቹ የመምህር እርማትን እንደሚመርጡ ምላሽ ሰጥተዋል (አባሪ “ሐ” ይመለከቷል)፡፡

የመጨረሻውና ሶስተኛው መሠረታዊ ጥያቄ “በግለ-ቢጤ እርማት ላይ ተማሪዎቹ የሚሰጧቸው አስተያየቶች ምን ይመስላሉ?” የሚል ነበር፡፡ በዚህም ተማሪዎቹ በተለዋወጧቸው የእርማት ቅጾች ላይ የተገኘው መረጃ ተማሪዎቹ የተሟላና በሳል የሆነ ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት የአቅም ውሱንነት እንዳለባቸው መረዳት ተችሏል (አባሪ “መ” ይመለከቷል)፡፡

የውጤት ማብራሪያ

የጥናቱን መረጃዎች በመተንተን ረገድ በመጀመሪያ የታየው የድርሰት ፈተናው ውጤት ነው፡፡በዚህም በሙከራ ቡድን አንድና በሙከራ ቡድን ሁለት ድርሰት በመጻፍ ችሎታ መካከል ንጽጽር ተደርጓል፡፡ ከንጽጽሩ የተገኘው ውጤት የሙከራው ቡድን ድህረ ልምምድ የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤት ከሙከራ ቡድን ሁለት የድርሰት ፈተና አማካይ ውጤት አንሶ ጉልህ ልዩነት (P=0.000) አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የግለ-ቢጤ እርማትን ከተጠቀሙት ተማሪዎች ይልቅ የመምህር እርማትን ያገኙ ተማሪዎች ድርሰት መሻሻል እንደታየበት የውጤት ትንተናው አመላክቷል፡፡ ይህም ከMesfin (2004) ፣Italo (1999)፣ Tesfaye (1999)፣ ከኤፍሬም (2000)፣ Graner (1978) ከልሰው ካቀረቧቸው የጥናት ግኝቶች ጋር ተቃርኖ ሲያሳይ፣ ከMaarof et al. (2011) እና Conur and Senavegin (1994) የጥናት ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት አሳይቷል፡፡

ድርሰትን በግለ-ቢጤ እርማት ስልት ወይም በመምህር እርማት ከማሳረም አንጻር የተማሪዎቹ ምርጫ የመምህር እርማት እንደሆነ የተገኘው ውጤት ከMaarof et al. (2011)፣ እንዲሁም Hyland & Hyland (2006) ዋቢ ካደረጓቸው ከLee (2004)፣ Ferris & Roberts (2001)፣ Hyland (1998) እና Ferris (1995) የጥናት ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት ሲያሳይ፣ ከተሻገር (2001) እና ከMesfin (2004) የጥናት ውጤት ጋር ግን ተቃርኖ አሳይቷል፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎቹ የሚሰጧቸው አስተያየቶች የተማሪዎችን ድርሰት ለማሻሻል የማይረዱ፣ ብስለት የሌላቸው እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ጠቁሟል፡፡ ይህም ግኝት ከFerris (2003) እና Graner (1987) የጥናት ግኝት ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት የግለ-ቢጤ እርማትና የመምህር እርማት ስልት የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያላቸውን አስተዋጽኦ በመፈተሽ ከሁለቱ የትኛው የተሻለ ሊሆን እንደሚችል ማሳየት ነበር፡፡

በዚህ መሠረት በመጀመሪያ ተጠኚዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተመርጠዋል፡፡ ተጠኚዎቹ 143 የሚሆኑ የፋሲለደስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ለጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያነትም የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና፣ ምልከታና ቃለመጠይቅ ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

ለጥናቱ የተሰበሰቡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግም በግለ-ቢጤ እርማትና በመምህር እርማት በተለማመዱ ተማሪዎች መካከል በተደረገው ንጽጽር የግለ-ቢጤ እርማትን ከተጠቀሙ ተማሪዎች ይልቅ የመምህር እርማት ያገኙ ተማሪዎች ድርሰት መሻሻል እንደታየበት በስታትስቲክስ (P=0.000) ጉልህ ልዩነት ተመዝግቧል፡፡

በመቀጠል ድርሰትን በግለ-ቢጤ እርማት ወይም በመምህር እርማት ስልት ከማሳረም አንጻር የተማሪዎቹ ምርጫ ምንድነው? የሚለውን ለማየት ተሞክሯል፡፡ በዚህም ተማሪዎቹ የመምህር እርማት ማግኘትን እንደሚመርጡ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

ሌላው በዚህ ጥናት የውጤት ትንተና ላይ ትኩረት ተሰጥቶት የነበረው ጉዳይ ተማሪዎቹ የሚሰጧቸው አስተያየቶች ምን ይመስላሉ የሚለው ነበር፡፡ በዚህም ተማሪዎቹ የሚሰነዝሯቸው አስተያየቶች ጥልቅና መሠረታዊ እንዳልሆኑ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት የግለ-ቢጤ እርማትና የመምህር እርማት ስልት የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያላቸውን አስተዋጽኦ በመፈተሽ ከሁለቱ የትኛው የተሻለ ሊሆን እንደሚችል ማሳየት ነበር፡፡ ከዚህ በመነሳትም የጥናቱን ትንተናና ውጤት መሠረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው በግለ-ቢጤ እርማትና በመምህር እርማት በተለማመዱ ተማሪዎች መካከል በተደረገው ንጽጽር የግለ-ቢጤ እርማትን ከተጠቀሙ ተማሪዎች ይልቅ የመምህር እርማት ያገኙ ተማሪዎች ድርሰት ጉልህ መሻሻል አሳይቷል፡፡ ይህም ውጤት መምህራን የሚሰጡት እርማት ከግለ-ቢጤ እርማት በተሻለ የተማሪዎችን

ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ያጎለብታል የሚል አንድምታ ሊሰጥ ይችላል፡፡

በጥናቱ ውጤት መሠረት ድርሰትን በግለ-ቢጤ እርማት ወይም በመምህር እርማት ስልት ከማሳረም አንጻር ተማሪዎቹ የመምህር እርማትን ማግኘት እንደሚመርጡ ታይቷል፡፡ ይህም ተማሪዎች ቢጤዎቻቸው በሚሰጧቸው አስተያየት እምነት እንደሌላቸውና የመጻፍ ችሎታቸውን ለማጎልበት የመምህሩ እርማት የላቀ ድርሻ አለው የሚል አመለካከት ተማሪዎቹ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎቹ የሚሰጧቸው አስተያየቶች ጥልቅና መሠረታዊ እንዳልሆኑ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ ይህም ውጤት ተማሪዎቹ ድርሰት ለማሻሻል የሚረዳ በሳል የእርማት አስተያየት ለመስጠት የአቅም ውስንነት እንዳለባቸው ስለሚያሳይ፣ ተማሪዎች ለሚጽፉት ድርሰት እርማት መስጠት ያለባቸው መምህራን ናቸው የሚል አንድምታን ይሳያል፡፡

የዋቢዎች ዝርዝር

ማረው ዓለሙ። (1996)። በሳል ድርሰት ማስተማሪያ። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ሰለሞን ተሰማ፡፡ (1987)፡፡ "የብጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት (ያልታተመ የኤም.ኤ. ቴሲስ)፡፡

ተመስገን አመራ። (1996)። "የመፃፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት የቢጤ እርማት ሚና።" ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ የመጀመሪያ ድግሪ ሟሟያ (ያልታተመ)።

ተሻገር አስማረ፡፡ (2001)፡፡ "የግል እርማት ስልት ውጤታማነት ጽሑፍን በመማር ማስተማር ሂደት-በአዲስ አበባ የአንደኛ ዓመት/ቅድመ ምረቃ መርሃ ግብር/ የአማርኛ ቋንቋና ስነጽሑፍ ተማሪዎች፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት (ያልታተመ የኤም.ኤ. ቴሲስ)፡፡

ኤፍሬም ጥሩነህ፡፡ (2000)፡፡ "የመፃፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት የግልና የቢጤ እርማት ያላቸው ሚና፡፡" ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ድህረ ምረቃ ፕሮግራም (ያልታተመ የኤም.ኤ. ቴሰስ)፡፡

Allwright, D., and Bariley, K. M.(1991). *Focus on the Language Classroom: An Introduction to Classroom research for language teachers.* Cambridge: Cambridge University Press.

Ancker, W.(2000). "Errors and Corrective Feedback: Updated Theory and Classroom Practice." *English Teaching Forum,* 38(4), 20-24

Asres Nigus.(2005). "*An Exploration of the Written Error Treatment Practices of the Intermediate Writing Skills Instructors of Bahir Dar University.*"A.A.U: Unpublished MA thesis.

----------------.(2001)."*An Investigation in to the Treatment of Oral Errors by English Teachers.*" In Partial Fulfillment of B.Ed. B.D.U: unpublished B.A thesis.

Atkins, J.,Hailom Banteyrga and Nuru Mohammed.(1996).*Skills Development Methodology(Part2*). Addis Ababa: Addis Ababa University.

Berg, E.(1999). "The Effects of Trained Peer Response on ESL Students' Revision Types and Writing."*Journal of Second Language Writing,* 8(30), 215-241.

Brookes, A., and Grundy,P.(1990). *Writing for Study Purpose. Great Britain*: Cambridge University Press.

Brown, H.D.(1994).*Principles of Language Learning and Teaching*: Longman.

Byrne, D.(1988). *Teaching Writing Skills.* Singapore: Longman Group U.K Limited.

Caulk, N.(1994). "Comparing Teacher and Students Responses to Written Work."*TESOL Quarterly,* 28(1), 181-187.

Conur, B and Senavegin, K. (1994). The Role of Self, Peer and Teachers Feedback on Students Writing Skills. *TESOL Quarterly,* 10(3), 321-326.

Edge, J. (1989).*Mistakes and Correction.* London: Longman.

Ferris, R.D.(2003). *Response to Student Writing Implication for Second Language Students.* London: California State University.

Gabrielatos, C.(2002). "EFL *Writing: Product and Process*." (http://temarinet.com/te marinet-library/)

Graner, H. M.(1987). "Revision Workshops: An Alternative to Peer Editing Groups." *The English Journal,* 76(3), 40-45.

Harmer, J.(1991). *The Practice of English Language Teaching*(new edition). London and NewYork: Longman Limited.

Heaton, J.B.(1990). *Classroom Testing.* USA: Longman Inc.

Hedge, T.(1990). *Writing. Oxford:* Oxford University Press.

Hedgock, J., and Lifkowitz, N.(1992). "Collaborative Oral/Aural Revision in Foreign Language Writing Instruction."*Journal of Second Language Writing,* 1(3), 255-276.

Hyland, K., and Hyland,F.(2006). "Feedback on Second Language Students Writing."*Language Teaching, 3*9,83-101.

Italo Beriso.(1999). "*A Comparison of the Effectiveness of Teacher versus Peer Feedback on Addis Ababa University Students' Writing Revisions.*"(Unpublished doctoral dissertation). A.A.U.

Jacobs, G.(1988). "Co-operative Goal Structure: A Way to Improve Group Activities." *ELT Journal,* 42(2), 97-101.

Jacobs, H., & etal.(1981). Testing ESL Composition: A Practical Approach. Massachusetta: Newbury House Publisher.

Johnson,K.(1988). "Mistake Correction."*ELT Journal,* 42(2), 97-101.

Karegianes, M.L., Ernest T. P., and Pflaum,S.(1980). "The Effect of Peer Editing on the Writing Proficiency of Low Achieving Tenth Grade Students."J*ournal of Educational Research,* 73(4),203-206.

Littelwod, W.(1981).*Communicative Language Teaching: An Introduction.* Cambridge: Cambridge University Press.

Maarof, N., Yamat, H. & Li, K.L.(2011).“*Role of Teacher, Peer and Teacher-Peer Feedback in Enhancing ESL Students' Writing.*”

Madsen, H.S.(1983). *Techniques in Testing.* Hong kong: Oxford University Press.

Makino, T.V.(1993). “Learner Self-Correction in EFL Written Composition.” *ELT Journal,* 47(4), 337-341.

McArthur, T.(1983). *A Foundation Course for Language Teachers.* Great Britain: Cam bridge University Press.

Mendonca,C.O., and Johnson, K.E.(1994). “Peer Review Negotiations: Revision Activities in ESL Writing Instruction.” *TESOL Quarterly,* 28(4), 745-768.

Mesifin Abera.(2004). “*An Investigation of the Level of Effectiveness of Peer Correction versus Self Correction on Grade 12 Students: Writing with a Particular Reference to Menlik II Secondary School.*” (Unpublished master's thesis).A.A.U.

Nelson, G.L., and Murphy, J.(1993). “Peer Response Groups: Do L2 Writers Use Peer Comments in Revising Their Drafts?” TESOL Quarterly, 27(1), 135-141.

Nelson, G.L., and Carson, J.(2003). “Cultural Issues in Peer Response: Revising Culture.” (http://temarinet.com/temarinet-library/)

Norrish, J.(1983). *Language Learners and Their Errors.* London: Macmillan Publishers Ltd.

Nunan, D.(1989). *Designing Tasks for the Communicative Classroom.* Cambridge: Cambridge University Press.

Pianko, S., and Radizik, A.(1980). “The Student Editing Method.”*Theory into Practice*, 19, 220-224.

Raimes, A.(1991). “Out of the Woods: Emerging Traditions in the Teaching of Writing.” *TESOL Quarterly,* 25(3),407-430.

------------.(1987). *Exploring Through Writing: A Process Approach to ESL Composition.* New York: St.Martin's Press, Inc.

------------.(1983).Techniques in Teaching Writing. Oxford: Oxford University Press.

Roessler, M.(1983). “Focus on Feedback.” In Stephen Tehudi(ed.). *Writing Teachers: What We Say About What We Do*(pp.158-165). Rochester: Michigan Council of Teachers of English.

Tesfaye Solomon.(1999). “Teacher Correction versus Learner Self Correction of Written Errors.” In Zerihun Asfaw and Derje Gebre (eds.). *Proceeding of the 9th Annual Conference of the Institute of Language Studies* A.A.U.

Tilahun Bekele.(2003).“Process Writing and the Role of Teachers in Giving and Facilitating Feedback.” In Proceedings of the 14thAnnual Conferencing of the Institute of Language Studies Addis Ababa University.

Ur, P.(1999). *A Course in Language Teaching: Practice and Theory*. Cambridge: Cambridge University Press.

Witbeck, M.C.(1976). “Peer-Correction Procedures for Intermediate and Advanced ESL Composition Lessons.”*TESOL Quarterly,* 10(3), 321-326.